Amharic

# በአውስትራሊያ ውስጥ ስለአካል ጉዳተኝነት ያለዉ ግንዛበ

## ተጨባጭ መረጃ ቅጽ 1

**ይህ ተጨባጭ መረጃ የተዘጋጀው ለአካል ጉዳተኞች ሙብት መከበር በቆመዉ እና እንዲሁም የሚያስፈልጋቸዉ መሰረታዊ ፍላጎት እንዲማላ በሚሰራ AMPARO በተባለ ድርጅት ሲሆን ከተለያየ ባህል እና ቋንቋ ለመጡ ልዩ ልዩ ማህበረሰቦች ስለአካል ጉዳተኝነት በቋንቋቸዉ የተተረጎመ መረጃን ለማቅረብ ነው።**

1. አካል ጉዳተኝነት ምንድነው?
2. አካል ጉዳተኝነት በአውስትራሊያ
3. የአካል ጉዳተኝነት ዓይነቶች
4. በጊዜ የእርዳታ ድጋፍ ማግኘት
5. የሚፈልጉትን ድጋፍ ስለማግኘት
6. እርዳታ የት እንደሚገኝ
7. በአውስትራሊያ ለአካል ጉዳተኛ በሚሰጡ
   አገልግሎቶች ላይ የሚደረጉ አዳዲስ ለዉጦች
8. አስተርጓሚዎች የሚሰጡትን ኣገልግሎት ማግኘት
9. ስለችግሮዎ ለመናገር እርዳታ ስለማግኘት



## 1. አካል ጉዳተኝነት ምንድነው?

ሰዎች የአካል ጉዳት ሊኖርባቸው የሚችለዉ ሰዎቹ እራሳቸውን ለመንከባከብ፣ በእግር ለመጓዝ ወይም ባሉበት አካባቢ ለመንቀሳቀስ፣ ለመስማት ወይም ለማየት ወይም በግልጽ ለማሰብ ወይም ለመማር ከባድ ሆኖ ካገኙት ነው። እነዚህ ሰዎች የእለት ተእለት ተግባራትን ለማከናወን ችግር ሊሆንባቸው ይችላል።

***በኣንድ ሰዉ ህይወት አካል ጉዳተኝነት*** ሊከሰት የሚችለው በአደጋ፣ እጅግ አሳዛኝ በሆነ ገጠመኝ፣ በበሽታ ወይም ከኣንድ የአካል ጉዳተኝነት ሁነታ ጋር አብሮ በመወለድ ነዉ። አካል ጉዳተኝነት ኣብዘኛዉን ጊዜ ለረጅም ጊዜ የሚቆይና ቀጣይነት ያለዉ እስከ ህይወት መጨረሻ አብሮ የሚቆይ ነው። ስለዚህ አካል ጉዳተኝነት ለተወሰነ ወራት እንደምንታመመዉ በሽታ ዓይነት ወይም፣ በቀላሉ ሊድን እንደሚችል የአጥንት ስብራት አይደለም።

የኣካል ጉዳተኞች ችሎታቸው ለሎች ሰዎች ስለእነሱ በሚያስቡት (ስለእነሱ ባላቸዉ አመለካከት) ምክንያት እና በሚኖሩበት ኣካባቢ ለምሳለ  በቤታቸው፣ በሥራ ቦታቸዉ ወይም በማህበረሰብ ዉስጥ በሚያደርጉት እንቅስቃሰ ፤ የህዝብ መጓጓዣ መጠቀም መቻላቸዉና አለመቻላቸው እና  በማህበረሰባቸው ዉስጥ በሚደረግላቸው እንክብካቤ ተጽእኖ ሊደርግባቸው ይችላል።

## 2. አካል ጉዳተኝነት በአውስትራሊያ

በአውስትራሊያ ውስጥ የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች ከሌሎች በማህበረሰብ ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር ተመሳሳይ መብቶች እና ለሎች ሰዎች ማድረግ የሚችሉትን ተመሳሳይ ነገሮች ማድረግ ይፈቀድላቸዋል። ለምሳሌ፡ አግባብነት ያለው እንክብካበ የማግኘት፣ የመማር፣ የመሥራት፤ እንዲሁም የት እንደሚኖሩ፣ እና እንዴት ህይወታቸውን እንደሚኖሩ የመምረጥ ሙብት አላቸው።

የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች ጥሩ ኑሮ ሊኖሩ ይችላሉ፤ ያላቸውን የህይወት እቅድና ህልም ሊያሳኩ ይችላሉ፤ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ በመካተት አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ። የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች ብዙ ጥንካሬና ብቃት ያላቸው እና አዳዲስ ክህሎቶችን የመማር አቅም አላቸው።

የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች በሁሉም መልኩ በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ኑሮ ውስጥ ለመካተት ይፈልጋሉ፤ እና ይህንን ለማድረግ እንዲችሉ የአውስትራሊያ ህጎች ይደግፉቸዋል። በአውስትራሊያ ውስጥ የአካል ጉዳት ያለበት ሰው ላይ የሚደረግ መድልዎ ህገ-ወጥ ነው።

አንድ ሰው የአካል ጉዳት አለበት ማለት  ያ ሰው ነገሮችን ለየት ባለ መልኩ ያደርጋቸዋል ማለት ነው፤ እና የአካል ጉዳት ያለባቸዉ ሰዎች ልዩ ልዩ እገዛ ወይም ድጋፍ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ምናልባት እርዳታ ሊፈልጉ የሚችሉት:

- ገላን ለመታጠብ
- ልብሳቸውን ለመልበስ
- ወደ አልጋ ለመውጣት እና ከአልጋ ለመውረድ
- ሰዎች በሚረዳዋቸው መልኩ ለመናገር
- ከገበያ እቃ ለመግዛት
- በማህበረሰብ ውስጥ ለመሳተፍ
- ወደ ሥራ ወይም ወደ ህክምና ቀጠሮ ለመጓዝ
- እንደ ተሽከርካሪ ወንበር/wheelchair መሳሪያዎችን ለመግዛት
- የመኖሪያ ቤታቸውን ለመንከባከብና ጥሩ ህይወት ለመኖር

# 3. አካል ጉዳተኝነት ዓይነቶች

## የአእምሮ ውስንነት

የአእምሮ ውስንነት ያለባቸዉ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲነጻጸሩ አዳዲስን ነገሮች ለመማር፣ ችግሮችን ለመፍታት፣ በአንድ ነገር ላይ ትኩረት ለማድረግ እና ነገሮችን ለማስታወስ የበለጠ ችግር ሊኖርባቸው ይችላል። የአእምሮ ውስንነት የተለመዱ ምክንያቶች -

- አብሮ ከአእምሮ ውስንነት ጋር መወለድ
- በእርግዝና ጊዜ በሚገጥሙ ችግሮች (ለምሳሌ፡ በቂ ኦክሲጅን አየር አለማግኘት)
- የጤና ችግሮች
- በቂ ምግብ ወይም ጥሩ የህክምና እንክብካቤ አለማግኘት

## አካላዊ ጉዳተኝነት

አካላዊ የአካል ጉዳተኝነት የአንድ ሰዉ የሰውነት አሠራሮች ወይም የመንቀሳቀስ አቅም ላይ ተጽእኖ ያደርጋል፤ ለምሳሌ፡ በእግር መሄድ ወይም ፊኛን/የሽንት ከረጢትን በመቆጣጠር ላይ ችግር ይፈጥራል። ወይም የተወሰነ የሰውነት ክፍል ላይ ተጸእኖ ሊያደርግ ይችላል ለምሳሌ፡ እግር ወይም እጅ አለመኖር። ለአካላዊ ጉዳተኝነት ብዙ ምክንያቶች አሉ፤ አንድ ሰው ከአካላዊ ጉዳተኝነት ጋር አብሮ ሊወለድ ይችላል፣ አደጋ ሲደርስበት ወይም በበሽታ ሳቢያ ሊከሰት ይችላል። የአከርካሪ መጎዳት፣ የአንጎል በሽታ እና ብዙ ውስጣዊ ብልቶች መዛባት በአካላዊ ጉዳተኝነት ዉስጥ ይካተታሉ።

## የአእምሮ ነርቭ አካል ጉዳተኝነት

የአእምሮ ነርቭ አካል ጉዳተኝነት አንጎል ለሌሎች የሰውነት ክፍሎች መረጃ የሚያስተላልፍበት እና ግንኙነት የሚያደርግበት መንገድ ላይ ችግር ይፈጥራል፤ ለምሳሌ፡ በመናገር፣ በማሰብ እና በመንቀሳቀስ ላይ ችግር ይፈጥራል። ሰዎች ከአእምሮ ነርቭ አካል ጉዳተኝነት ጋር አብሮ ሊወለዱ ይችላሉ፤ ከተወለዱም በኋላ በህይወት ቆይተው የአእምሮ ነርቭ አካል ጉዳተኛ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም በአደጋ ሳቢያ የአእምሮ ነርቭ አካል ጉዳተኛ ይሆናሉ።

### የአእምሮ ህመም

የእምሮ ህመም ያለባቸው ሰዎች የማሰብ፣ ስሜታቸውን የመግለጽ ወይም በባህርያቸው ላይ ችግር ሊኖርባቸው ሲችል ይህም ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ የመሥራት ወይም ኑሯቸውን የመኖር ብቃታቸው ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል። ለምሳሌ፡ አንድ ሰው በእለት ተእለት የኑሮ ህይወት ላይ ለመሳተፍ የሚያሰናክሉ ብዙ የጭንቀት መንፈስ ሊኖሩት ይችላል። ይህም ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ የመሥራት እና ህይወታቸውን ደስታን በሚሰጥ ሁኔታ እንዳይኖሩ ችግር ሊፈጥር ይችላል።

### የስሜት ህዋሳት ጉዳተኝነት

በዚህ ውስጥ የሚካተቱት የመስማት፣ የማየት ወይም የመናገር ችግሮች ናቸው።

### ከጊዜ በኋላ የሚመጣ የአንጎል ጉዳት

ከጊዜ በኋላ የሚመጣ የአንጎል ጉዳት የሚከሰተው ከተወለዱ በኋላ ነው። ከጊዜ በኋላ የሚመጣ የአንጎል ጉዳት በመኪና፣ በስፖርት ወይም በሌሎች አደጋዎች፣ በደም መርጋት፣ በአንጎል እጢ፣ በአልኮሆል፣ በአደገኛ እጽ ያላግባብ መጠቀም ወይም በመመረዝ ሊከሰት ይችላል። ከጊዜ በኋላ የሚመጣ የአንጎል ጉዳት የሚያስከትለው ችግር አነስተኛ እና ለአጭር ጊዜ የሚቆይ ወይም ከባድና እስከ ህይወት መጨረሻ ሊቆይ ይችላል።

### በልጅነት የሚከሰት የአእምሮ ችግር/ኦቲዝም

ኦትዝም ያለባቸው ሰዎች የቋንቋ ወይም የመግባባት እና ማህበራዊ ግኙኝነት ክህሎቶችን ለመማር ችግር ይኖርባቸዋል፤ ኦትዝም ያለባቸው ሰዎች ድምጽ ስሰሙ ፣ በእጅ ሲነኩ፣ አንድ ነገር ሲቀምሱ፣ አንድ ነገር ሲያሸቱ፣ ለመብራት ወይም የተለያዩ ቀለማትን ሲያዩ በጣም የቁጡነት ስሜት ሊኖራቸው ይችላል።

## 4. በጊዜ እርዳታ ስለማግኘት

ልጅዎ የአካል ጉዳተኝነት አለበት ብለው ካሰቡ በተቻለ ፍጥነት እርዳታ ማግኘት ልጁ በሚገባ እንዲያድግና እንዲሻሽል ሊረዳው ይችላል፡ ይህም ልጅዎ ካደገ በኋላ ብዙ እርዳታ ድጋፍ አያስፈልገዉም ማለት ነው።

በጊዜ እርዳታ ማግኘቱ ቤተሰቦች ልጆቻቸው ያለባቸዉን የአካል ጉዳተኝነትን እንድገነዘቡ እና ለልጆቻቸው ጥሩ እንክብካቤ እንድያደርጉላቸው ያግዛቸዋል።

## 5. የሚፈልጉትን ድጋፍ ስለማግኘት

አንዳንድ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው የሚፈልጉትን እርዳታ ለማግኘት ይቸገራሉ። ስለዚህ ስለአካል ጉዳተኝነት ማወቅና መረዳቱ አስፈላጊ ነው። አካል ጉዳተኝነት እንዳልዎ ወይም እንደለሎዎ ለማወቅ ከሀኪምዎት ጋር መነጋገር ይችላሉ። የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉ አገልግሎቶችና ድጋፎች አሉ።

## 6. እርዳታ የት እንደሚገኝ

በኲውንስላድ/Queensland ውስጥ የሚኖሩ ከሆነና እርስዎ ወይም የርስዎ ቤተሰብ አባል እርዳታ ካስፈለገ አሁን በስልክ ቁጥር 13 74 68 መደወልና ከአካል ጉዳተኝነት አገልግሎት የሆነ ሰው ስለርስዎ ሁኔታ እንዲያነጋግርዎት መጠየቅ ይችላሉ።

## 7. ለአካል ጉዳተኞች በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ የሚደረጉ አዳዲስ ለውጦች

የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው የሚፈለጉትን እርዳታ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ በሚቀጥሉት 3 ዓመታት ውስጥ ታላቅ ለውጦችና መሻሻሎች ይኖራሉ። ወቅታዊ መረጃን ለማግኘት አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር/National Disability Insurance Scheme ድረገፅ www.ndis.gov.au ላይ ማየት ወይም በስልክ ቁጥር 1800 800 110 ለነሱ መደወል፡ አስተርጓሚ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር 131 450 መደወል ይቻላል።

## 8. አስተርጓሚ ነው የሚፈልጉት ወይንስ የተተረጎመ ጽሁፋዊ መረጃ?

በኩዊንስላንድ አስተዳደር መንግሥት/Queensland State Government የገንዘብ እርዳታ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ድጋፍ የሚያደርጉ አገልግሎቶች በሙሉ አስፈላጊ ከሆነ አስተርጓሚዎችን ማቅረብ አለባቸው፤ እርስዎም አስተርጓሚ እንዲቀናጅልዎ መጠየቅ ይችላሉ። እንዲሁም አገር አቀፍ የአካል ጉዳተኝነት የመድህን ዋስትና አሰራር/The National Disability Insurance Scheme አስተርጓሚ ያቀርባል። **አስተርጓሚዎች ስልጠና ያገኙና የርስዎን መረጃ በምስጥር መጠበቅ አለባቸው።** እንዲሁም አገልግሎት አቅራቢዎች፤ እርስዎ በሚረዱት መንገድ መረጃዎችን መስጠት አለባቸው፤ ለምሳሌ፡ መረጃው በራስዎ ቋንቋ እንዲተረጎም ሊጠይቋቸው ይችላሉ።


## 9. ስለችግሮዎ ለመናገር እርዳት ስለማግኘት

**ምን እንደፈለጉ ለማነጋገር እርዳታ ከፈለጉ፤ ይህን ለማካሄድ አድቮከስ ድርጅት/advocacy agency እርዳታ ማግኘት ይችሉ ይሆናል።**

በኩዊንስላንድ/Queensland ውስጥ ማነጋገር የሚችሉት-

| | |
|---|---|
| AMPARO Advocacy *(Brisbane)* | 3369 2500 |
| Capricorn Citizen Advocacy *(Rockhampton)* | 4922 0299 |
| Gold Coast Advocacy | 5564 0355 |
| Independent Advocacy Townsville | 4725 2505 |
| Ipswich Regional Advocacy Service | 3281 6006 |
| Mackay Advocacy Inc | 4957 8710 |
| Queensland Advocacy Incorporated | 3844 4200 |
| Rights In Action Incorporated *(Cairns)* | 4031 7377 |
| Speaking Up For You *(Brisbane/ Caboolture)* | 3255 1244 |
| Sunshine Coast Citizen Advocacy | 5442 2524 |
| The Advocacy and Support Centre *(Ipswich)* | 3812 7000 |
| The Advocacy and Support Centre *(Toowoomba)* | 4616 9700 |
| People with Disability Australia | 1800 422 015 |

(*Bundaberg, Fraser Coast, Logan, Mt Isa, Sunshine Coast)*



## ቅሬታ ለማቅረብ ይቻላል።

ያስታውሱ፤ አንድን ድርጅት ለማነጋገር ከተነገርዎት እና ያ ድርጅት ካልረዳዎት እንደገና ተመልሶ በመሄድ የተሻለ እርዳታ እንዲያቀርብልዎት መጠየቅ፤ ወይም ቅሬታ ማቅረብም ይቻላል።

በባህል ወይም አካል ጉዳተኛ በመሆንዎ አድልዎ ተደርጎብኛል የሚል ስሜት ካደረብዎት ለኩዊንስላንድ ጸረ-አድልዎ ኮሚሽን/Queensland Anti-Discrimination Commission በስልክ ቁጥር 1300 130 670 ደውሎ ማነጋገር ይችላሉ።

---

ይህ መረጃ የተዘጋጀው ለአካል ጉዳተኞች መብት መከበር በቆመዉ እና እንዲሁም የሚያስፈልጋቸዉ መሰረታዊ ፍላጎት እንዲሟላ በሚሰራ ማህበር/AMPARO Advocacy Inc. ይህ መረጃ ተዘጋጅቶ ስታተም በጊዜ ትክክለኛ መረጃ መሆኑን ለማረጋጥ መደረግ ያለበት ቅንቃቀ ሁሉ ተደርግል። ይህ ዝርዝር መረጃ ግቡ አጠቃላይ መግለጫ ለመስጠት ተብሎ የቀረበ ሲሆን አሁን ባሉበት ሁኔታ ትክክለኛ፣ ወቅታዊ ወይም የተጠናቀቀ ላይሆን ይችላል። በበለጠ በግልዎ ምክር ቢያገኙ በጣም ይመረጣል።